## የወኪሎቻችን በፍትህ እጦት መጉላላት እፎይታው እንዲያበቃ ያስገድዳል!

ሐሙስ ሚያዝያ 2/2006

ከህግ የበላይነት ይልቅ የደህንነትና የመንግስት ሐይሎች ፍላጎት ተፈጻሚ በሚሆንበት የተቃወሰ የፍትህ ስርአት ውስጥ ንጹሀንን ማጉላላትና ፍትህን ማተጓጎል የተለመደ ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ቀድሞውንም ለህዝብ የሚታገሉ ንጹሀን ለእስር የሚበቁት በስርአቱ ፖለቲካ አቀንቃኞች ፍላጎት እንጂ ተጠርጥረዋል በተባሉበት ወንጀል ሊያስጠይቃቸው የሚያስችል ማስረጃ አለመኖሩ ነው፡፡

በተቃወሰው የአገራችን የፍትህ ስርአት ውስጥ ወኪሎቻችን በሐሰት ክስ እየተጉላሉ እና የፍርድ ሂደቱም እንዲጓተት እየተደረገ ቆይቷል፡፡ በህዝብ ላይ እየቀለዱ ያሉት የፍትህ አጣማሚ አካላትም ለዚህ ኢ-ፍትሀዊ ተግባራቸው ሰበቦችን መደርደርና የሀሰት ምክንያቶችን መስጠትን ልማዳቸው አድርገውታል፡፡ ካሁን ቀደም ‹‹ላም ባልዋለችበት ኩበት ለቀማ›› እንዲሉ ኢቲቪ በልብ ወለድ ደራሲዎቹ አማካኝነት የሚያዘጋጀውን አይነት ድራማ የሚሰሩና ንጹሀን ላይ በሐሰት የሚመሰክሩ የፍርድ ቤት ተዋናዮችን ለማዘጋጀት ጊዜ የሚወስድበትን ጊዜ በተለያዩ የህግ ቋንቋ ለበስ ሰበባ ሰበቦች ችሎት ሲያጓትቱ ቆይተዋል፡፡ አሁን ደግሞ መሪዎቻችን መከላከያዎቻቸውን ሲያሰሙ በርካታ ሰበቦች እየተፈጠሩ ችሎቱ እንዲጓተት እየተደረገ ነው፡፡ ከአንድ ምንጭ የሚቀዱት ዳኞቹ እና አቃቤያነ ህግጋቱ ዋነኛው ተልእኳቸው ማለቂያ በሌላቸው ጊዜ መግዣ ሰበቦች የፍትህ ፈላጊዎችን ተስፋ ለማቀጨጭ ነው፡፡ በዚህም ‹‹የሙስሊሙ ማህበረሰብ ተወካዮችና የወከላቸው ህዝብ ተሰላችቶ ትግሉን ትቶ እጁን አጣጥፎ ይቀመጣል›› የሚል ቀቢጸ ተስፋ ሰንቀዋል፡፡

ይህንን ታስቦበትና ሆን ተብሎ እየተፈጸመ ያለ ድርጊት፣ እንዲሁም ከበስተጀርባ ያለውን ስውር ዓላማ ህዝበ ሙስሊሙ አስቀድሞ ያወቀውና የተገነዘበው በመሆኑ እንደእስካሁኑ ሁሉ ያሳየውን ቆራጥነት አጠናክሮ በመቀጠል በደለኞችን ማሳፈር፣ ዓላማቸውንም ማክሸፍ ይጠበቅበታል፡፡ ተወካዮቻችንን መታደግና መደገፍ፣ መስጂዶቻችንን እና መድረሳዎቻችንን ለመጠበቅ መታገል ለዲናችን ዘብ መቆም ነው፡፡ እኛ በበረታን ቁጥር በደል ፈጻሚዎችን በመታገል ውሎ አድሮ ፍትህ ከአላህ የምናገኝበትን እለት እየተቃረብን ስለመሆናችን መጠራጠር የለብንም!

አቋማችን አሁንም እንደህዝብ ግልጽ ነው፡፡ መንግስት ሰላማዊ የህዝብ ወኪሎችን በሐሰት የሽብር ክስ ማጉላላትና ማንገላታት፣ እንዲሁም በፍትህ እጦት ማሰቃየቱን በቀጠለበት በዚህ ወቅት የእፎይታው ጊዜ ማብቃቱ የግድ የማይሆንበት ምክንያት የለም! የሚቀዘቅዝ ትግልም አይኖርም፤ ድልም ከአላህ እንጂ ከሌላ አይደለምና!!!

ትግላችን እስከድል ደጃፎች ድረስ ይቀጥላል!

ድምጻችን ይሰማ!
አላሁ አክበር!

## የትግል ቁርጠኝነትን ያስመሰከረ ታላቅ ተቃውሞ!



አርብ ሚያዝያ 3/2006

የዛሬው ጁምዓ ተቃውሞ ከታወጀ ሰአት ጀምሮ በማህበራዊ ሚዲያዎችና በበራሪ ወረቀቶች ከፍተኛ የሆነ ቅስቀሳ ነው ሲደረግ የነበረው፡፡ ተቃውሞው የተጠራው ውድ ኮሚቴዎቻችን ለቀረበባቸው የተቀነባበረ የሀሰት ክስ መከላከያ እያቀረቡ ሳለ እንደመሆኑ ለእነሱ ያለንን አጋርነት ለመግለጽና በፍርድ ቤትም እያሳዩት ባለው የዓላማ ጽናትና ቆራጥነት መኩራታችንን ለመግለጽ እንደመሆኑ ህዝቡ ዘንድ በከፍተኛ ተነሳሽነትና ገጉት ነው ሲጠበቅ የነበረው፡፡

በአዲስ አበባ ህዝበ ሙስሊሙ ዛሬ ወደ ታላቁ አንዋር መስጂድ መጉረፍ የጀመረው በማለዳ ነበር። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፖሊሶችና ደንብ አስከባሪዎች መስጂዱ ሞልቶ ህዝብ መንገድ ላይ ማንጠፍ ሲጀምር ህዝቡን ለመከልከል በመሞከር ሲተናኮሱ ተስተውለዋል። ታላቁ አንዋር መስጂድ በሁሉም አቅጣጫ በከፍተኛ ህዝብ ተሞልቶ የነበረ ሲሆን ህዝበ ሙስሊሙ በተለመደ ጨዋነቱ ትንኮሳውን ንቆ በማለፍ ዕለቱ በሰላም እንዲልያልፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል።

የጁምዓ ሰላት እንደተጠናቀቀ በወጣው መርሃግብር መሰረት ሁሉም አጠገቡ ካለው ሰው ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞ ከፍ በማድረግ የማይናጋውን አንድነቱንና ሁሉም በአንድ ልብ የኮሚቴው አጋር መሆኑን ውብ በሆነ ሁኔታ ዳግም አሳይቷል፡፡ በመቀጠልም ‹‹ፍትህን ተነፍገን ትግላችን አይቆምም!!›› የሚል ፅሁፍ የታተመባቸውና በእጅ የተጻፈባቸውን ነጫጭ ወረቀቶችን ከፍ አድርጎ በማሳየት ህዝበ ሙስሊሙ መብቱ እስኪከበር ድረስ ከመታገል ወደ ኋላ እንደማይል ቃሉን ሰጥቷል፡፡ በመጨረሻም አላህ ኮሚቴዎቻችንን ነጻ እንዲያወጣልንና ድልንም እንዲያጎናጽፈን ዱዓ ተደርጎ በሰላም ተበትኗል፡፡ የዛሬዋ ጁምዓ የሴቶች ተሳትፎና ሚና ከፍ ብሎ የተስተዋለባት ታላቅ ቀን ሆናም አልፋለች።

ከአዲስ አበባ ወጣ ስንል በሻሸመኔ አል ሂከም መስጂድ እጅግ ደማቅ ተቃውሞ ተከናውኗል፡፡ ልክ እንደ አዲስ አበባው ሁሉ ተቃውሞው በወጣው መርሃግብር መሰረት የተከናወነ ሲሆን የተለያዩ መፈክር የያዙ ወረቀቶችም ከፍ ብለው ታይተዋል፡፡ በተለያዩ የከተማዋ መስጂዶችም ለኮሚቴዎቻችንና ለኡስታዞቻችን ዱአ ተደርጓል።

ህዝበ ሙስሊሙ ዛሬም ሆነ ላለፉት ሁለት ዓመታት ሲያካሂዳቸው የነበሩት ደማቅ ተቃውሞዎች የሚያስተላፉት መልእክት ግልጽና ቀላል ነው፡፡ ህዝበ ሙስሊሙ ህገ መንግስታዊና ሰብአዊ መብቶቹን ያውቃል፤ ጠንቅቆም ይረዳል፡፡ ይህን መብቱን ለማስከበርም መታገል ብቸኛው አማራጭ መሆኑን አሳምሮ ያውቃል፡፡ ላለፉት ሁለት ዓመታት ሲያደርገው የቆየውም ይህንኑ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ በትግል መድረኩ ደግሞ ሰላማዊና በሳል በሆነ መልኩ ሲመሩት በነበሩት ድንቅ መሪዎቹ ላይ ያለው መተማመን እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ መሪዎቹ የሰላም አምባሳደሮች መሆናቸውን ለሰላም ባስገቡት ቃል ኪዳን መስክሮ ያረጋገጠው ሐቅ ነውና የሀሰት ክስ ሊገዛው አይችልም፡፡

በግፈኞች እጅ በሀሰት የሽብር ክስ ችሎት የቀረቡት ጀግኖቹን ንጽህና ለመመስከር ከማንም በላይ ግንባር ቀደም ተሰላፊ መሆኑን ህዝበ ሙስሊሙ በተደጋጋሚ አሳይቷል፡፡ በዛሬው ደማቅ ተቃውሞም የካንጋሮው ፍርድ ቤት በጀግኖቹ ላይ ለሚያደርሰው ተደራራቢ በደል ቁብ ሳይሰጥ አጋርነቱን የሚገልጽ መሆኑን ነው ያንጸባረቀው፡፡ የሀሰት ፕሮፓጋንዳ የማይበግረው፣ የሀይል እርምጃ የማያደናቅፈው፣ የበደል ጋጋታ የማይሰብረው ትውልድ ተሻጋሪ አጋርነት ማለት ይኸው አይደለምን?

አዎን! የዛሬው ተቃውሞ በመላው ሃገሪቱ ፍትህ ለተነፈጉ የትግላችን ባለቤቶች የተካሄደ የአጋርነት ማሳያ ተቃውሞ ነው፡፡ ዛሬም እንደቀደሙት ግዚያት በኮሚቴዎቻችን ላይ የሚፈፀመውን የፍትህ መዛባት ስናወግዝ ለኮሚቴዎቻችና ይመሩት በነበረው ትግል ምክንያት ለእስር እና ለእንግልት ለተዳረጉት ሁሉ የልብ ለልብ መልእክታችንን እያስተላለፍን ነው፡፡ መብትን በመጠየቃቸው እና መንግስታዊ ሃይማኖትን በመሸሻቸው ብቻ ‹‹አሸባሪ›› ተብለው በእስር የሚማቅቁትን ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ፍትህ እንጂ ህዝብ አልረሳቸውም፡፡ የዛሬው ተቃውሞ የዚህ አንዱ ማሳያ ነው፡፡

ክብር ለሙስሊሙ ኢትዮጵያዊ ይገባል! ከድጡ ወደ ማጡ የሆነው የመንግስት የመብት ጥሰት ሳይበግረው ፍፁም ባልተዛነፈ መልኩ ለመብት መታገል የሙስሊሙ ኢትዮጵያዊ ልዩ ጀግንነት እና ባህሪ ነውና ክብር ይገባዋል - ይህ ጀግና ትውልድ!!!

ትግላችን እስከድል ደጃፎች ይቀጥላል!

ድምፃችን ይሰማ!

አላሁ አክበር!

## የሙስሊም ተማሪዎች የመብት ጥሰት መባባሱ እፎይታው እንዲያበቃ ያስገድዳል!

አርብ ሚያዝያ 3/2006

ግዙፉ የኢትዮጵያ ሙስሊም ማሕበረሰብ በረጅሙ የሀገሪቱ ታሪክ ውስጥ በተፈራረቁ አምባገነን ገዥዎች ከፍተኛ ጭቆናና በደልን ሲያስተናግድ ቆይቷል። ቀደምት አባቶቻችን ያሳለፉት የጭቆና ታሪክ እንደየኖሩበት ዘመን ቅርፁ የሚለያይ ቢሆንም ሁሉንም ጭቆናዎች አንድ የሚያደርጋቸው መሠረታዊ ነጥብ ግን ሙስሊሙን ማህበረሰብ በዘመኑ እጅግ ጠቃሚ እና አስፈላጊ ከሚባሉ ማህበራዊ መብቶቹ እንዲገለል ማድረግ ነው። የመሬት ባለይዞታነት እጅግ ወሳኝ በነበረበት ዘመን ሙስሊሙ ማህበረሰብ በእምነቱ የተነሳ የመሬት ባለቤትነት መብት እንዳይኖረው እና ጭሰኛ እንዲሆን በአዋጅ ተደንግጎ ተፈፃሚ ተደርጓል።

የዘመናዊ ትምሕርት አስፈላጊነት ጭላንጭል እየታየ በመጣበት የንጉስ ሐይለስላሴ ዘመን ሙስሊሙ ማህበረሰብ ትምሕርት መማር ከፈለገ በየትምሕርት ቤቱ በግዴታ የማያምንበትን እምነት እንዲማር እና የከፍተኛ ትምህርት ደረጃ ከደረሰ ደግሞ እምነቱን እንዲቀይር፣ ያ ካልሆነ ግን እስልምናውን እና የሙስሊም ስሙን ይዞ ዩኒቨርስቲ መግባት እንዳይችል ተደርጓል፤ በጣት የሚቆጠሩ ጥቂት ተማሪዎች ብቻ እምነታቸውን በውስጣቸው ደብቀው እና ስማቸውን እየቀየሩ የከፍተኛ ትምህርት እድልን ማግኘት ችለዋል።

ኋላ ላይ በደርግ ዘመን ሙስሊሙ ማሕበረሰብ አካዳሚክ ትምሕርት የመማር መብት ተሰጥቶታል። አሁን በስልጣን ላይ ያለው እና ሙስሊሞችን ለከፋ በደል እየዳረገ የሚገኘው የኢህአዴግ መንግስት ግን ይህንን የመማር መብት በስልታዊ መንገድ መሸርሸር ተያይዞታል፡፡ በተዛዋሪ ሙስሊሙን ማህበረሰብ ከትምህርት ማግለል እና የድንቁርና እና የመሀይምነት ተምሳሌት ማድረግን በመመሪያ ደረጃ አርቅቆ በመሰናዳት ላይ ይገኛል። ገና ላልፀደቀው መመሪያ መሞከሪያነትም በርካታ ሙስሊም ተማሪዎችን ከትምህርት ገበታቸው እንዲሰናበቱ ተደርጓል። በ2005 የትምህርት ዘመን ከባህርዳር ዩኒቨርስቲ ብቻ ከአምስት መቶ /500/ በላይ ሙስሊም

ተማሪዎች በእምነታቸው የተነሳ ከትምሕርት ገበታቸው እንዲሰናበቱ ተደርጓል። ጫናውን ተቋቁመው ትምህርታቸውን መግፋት የመረጡትን ደግሞ መላውን ሙስሊም እንደሚያሸማቅቁት አክራሪ እና አሸባሪ በሚል የስነ ልቦና ጫና ያደርሳሉ፡፡ ብዙዎቹንም ለእስር ዳርገዋል፡፡ በሀገሪቱ ውስጥ ባሉ የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ በሙስሊሞች ላይ ብቻ ተነጣጥረው የሚፈፀሙ በደሎችን እና የማግለል ተግባራትን ስንመለከት በእርግጥም ኢትዮጵያዊው ሙስሊም እንደ አዬዎቹ ዘመን የዜግነት መብቱን በስልታዊ መንገድ እየተነፈገ መሆኑን እንረዳለን፡፡

የዜጎቿ እኩሌታ የሚሆነው የማህበረሰብ ክፍል ከትምሕርት ተገልሎ መሐይም እንዲሆን የሚፈልግ አሰራር ባለበት ሀገር ውስጥ እድገት፣ ስልጣኔ እና ብልፅግናን አሳካለሁ ብሎ መኳተን ከንቱ ምኞት ከመሆን በዘለለ መሬት ላይ የሚፈጥረው ተጨባጭ ለውጥ አይኖርም! ኢትዮጵያ እንደ ሀገር በሁለት እግሮቿ እንድትቆም ከተፈለገ የሁሉም ዜጎች መብት በእኩል ደረጃ ሊከበር እና ነፃነታቸውም ሊታወጅ ግድ ይላል! ይህንን ማሳካት የሚቻለው ደግሞ እስከ ድል ድረስ ታግሰን በምናደርገው መብትን የማስከበር ትግል ብቻ እና ብቻ ነው! መብት በመታገል እንጂ በልመና አይገኝምና የመንግስትን ሙስሊም ተማሪዎችን ከትምህርት ለማግለል እያደረገ ያለውን ስልታዊ ዘመቻ አጠናክሮ በቀጠለበት ወቅት እፎይታው ሊነሳ ግድ ይለናል፤ ድልም ከአላህ እንጂ ከሌላ አይደለምና!

ትግላችን እስከድል ደጃፎች ይቀጥላል!
ድምፃችን ይሰማ!
አላሁ አክበር!